ትምህርትሚኒስቴር
MINISTRY OF EDUCATION

*መስከረም 22፣2016 ዓ.ም*

**በሀገር አቀፍ ደረጃ ለመጀመሪያ ጊዜ የሚሠጠው ብሄራዊ የድህረ ምረቃ ትምህርት መግቢያ ፈተና ከመስከረም 28-30 /2016 ዓ.ም በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍል በሚገኙ የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ እንደሚሰጥ የትምህር ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡**

በሀገር አቀፍ ደረጃ ለመጀመሪያ ጊዜ የሚሠጠው ብሄራዊ የድህረ ምረቃ ትምህርት መግቢያ ፈተና መስከረም 28-30/2016 ዓ.ም በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍል በሚገኙ የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ እንደሚሰጥ የትምህር ሚኒስቴር አስታውቋል፡፡

በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች የሚገኙ አመልካቾች ከመስከረም 21-25/20016 ዓ.ም ድረስ በተዘጋጀው https://portal.aau.edu.et ድህረ ገጽ ላይ በመግባት የዩኒቨርሲቲዎች የቴሌ ብር አካውንትና ሌሎች መረጃዎችን የሚያገኙ ሲሆን የማመልከቻ ክፍያ 1000 ብር በTelebirr Super App በመጠቀም ክፍያ በመፈጸም ምዝገባ ማካሄድ ይቻላል፡፡

ከመስከረም 23-25/2016 ዓ.ም የልምምድ ፈተና (Mock Exam) የሚሰጥ ሲሆን ተፈታኞች በተመዘገቡበት ዩኒቨርሲቲ በመገኘት የተመዘገቡበትን User name እና Password በመጠቀም የልምምድ ፈተናወን መውሰድ ይችላሉ፡፡ የመግቢያ ፈተናውን የትምህርት ሚኒስቴር ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣የትምህርት ምርምር ኢንስቲትዩት የፈተና ማዕከል፣ኢትዮ ቴሌኮም እና የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች ጋር በመተባበር በዲጂታል ቴክኖሎጂ ተደግፎ ይሰጣል፡፡

በሁሉም የግልና የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መደበኛ እና መደበኛ ባልሆኑ የጊዜ መርሃ ግብሮች የሚሰጡ የ2ኛ እና 3ኛ ዲግሪ ትምህርት ፕሮግራሞችን ለመከታተል የብሄራዊ ድህረ ምረቃ ትምህርት መግቢያ ፈተና መውሰድና አስፈላጊውን የማለፊያ ውጤት ማስመዝገብ በቅድመ ሁኔታነት የተቀመጠ መሆኑን የትምህርት ሚኒስቴር አያይዞ አስታውቋል፡፡

በሚኒስቴር መስሪያቤቱ የከፍተኛ ትምህርት ልማት ዘርፍ ተወካይ ሚኒስትር ድኤታ ዶ/ር ሰለሞን አብርሃ በሁሉም የመንግስትና የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ የሚሰጡ የድህረ ምረቃ ትምህርት ፕሮግራሞች ውስጥ ገብቶ ትምህርት ለመከታተል ፍላጎት ያለው አመልካች የብሄራዊ ድህረ ምረቃ ትምህርት መግቢያ ፈተናን መውሰድና በትምህርት ሚኒስቴር የሚቀመጠውን የመግቢያ መቁረጫ ነጥብ ማሟላት እንደሚጠበቅበት ገልጸዋል፡፡

የፈተና ጥያቄዎቹ የሚያተኩሩት ችግር ፈቺ/problem solving/፣በጥልቀት ማሰብና ማሰላሰል /critical thinking/ እንዲሁም የሳይንስ ጽንሰ ሀሣቦችና መርሆች ላይ ትኩረት ያደረጉ እንደሚሆኑ ተገልጿል።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ ፈተናው ደህንነቱና ሚስጥራዊነቱ በተጠበቀ መልኩ የሚሠጥ ሲሆን የመግቢያ መቁረጫ ነጥብ የጥሬ ማርክ ውጤትን መሰረት ባደረገ መልኩ በትምህርት ሚኒስቴር የሚወሠን ይሆናል።

አጠቃላይ ፈተናው የሚያተኩረው የተፈታኞች ሂሣባዊ ትንተና፣ምክናያታዊ አስተሳሰብ፣ የቃልና የጹህፍ ክህሎት ለመመዘን የሚዘጋጅ በመሆኑ ተፈታኞች በዚሁ አግባብ ዝግጅት ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

ትምህርትሚኒስቴር
MINISTRY OF EDUCATION

**ብሄራዊ የድህረ ምረቃ ትምህርት መግቢያ ፈተና ዓላማ**

- በግል እና በመንግስት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ገብተው የድህረ ምረቃ ትምህርት በ2ኛ እና 3ኛ ዲግሪ የትምህርት ፕሮግራሞች ገብቶ ትምህርት ለመከታተል ፍላጎት ያላቸውን አመልካቾች ብቃት ለመመዘን ነው።

- ድህረ ምረቃ ትምህርት ፕሮግራሞች የሚገቡ ተማሪዎች ሂሣባዊ ትንተና (Quantitative reasoning) ፣ምክናያታዊ አስተሳሠብ (Analytical reasoning) ፣ የቃልና የጹህፍ ክህሎት ለመመዘን።

**የፈተና አስተዳደር**

- የመግቢያ ፈተናው ወጥ በሆነ መንገድ በአንድ የፈተና መተግበሪያ የሚከወን ነው፡፡
- ፈተናው ምርጫ ጥያቄዎችን የያዘ ነው፡፡
- 53 የፈተና ማእከላት እና 84 የፈተና ጣቢዎች ተዘጋጅተዋል፡፡
- በግማሽ ቀን ( ለሶስት ሠአታት) ውስጥ የሚጠናቀቅ ይሆናል
- አይነስውራን ተፈታኞች የቃልና ምክንያታዊ አስተሣሠብ ክህሎቶቻቸው ላይ ብቻ ያተኮሩ ፈተናዎችን ይወስዳሉ፤ በወሠዱትም ፈተና ከ100% ይመዘናሉ
- የድህረ ምረቃ ትምህርት ጥራትን ለማስጠበቅ በትምህርት ሚኒስቴር የተቀመጠ ቅድመ ሁኔታ ነው።
- ብሄራዊ የድህረ ምረቃ ትምህርት መግቢያ ፈተና ጥያቄዎች አመልካቾች መርጠው በሚያመለክቱበት የትምህርት መስክ ላይ ትኩረት ያደረገ አይደለም።

**ለፈተናው እንዴት ማመልከት ይቻላል?**

- ምዝገባ የሚከናወነው በድረ ገጽ ሲሆን https://portal.aau.edu.et ላይ ከመስከረም 21-25/20016 ማመልከት ይቻላል፡፡
- ለተጨማሪ መረጃ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ግራንድ ዌብሣይት እና Testing Centre_IER_AAU (https://t.me/aauGAT) በሚል የተከፈተውን የቴሌግራም ቻናልን በመጎብኘት እንዴት ማመልከት እንደሚቻል ማወቅ ይቻላል።

**የፈተና ውጤቱ የሚኖረው ፋይዳ**

- በትምህርት ሚኒስቴር የሚቀመጠውን የመግቢያ መቁረጫ ነጥብ ማሟላት
- ውጤቱ ለሁለት አመት የሚያገለግል መሆኑ

**የፈተና ውጤት**

- ሀሉም ተፈታኝ የማለፊያ ውጤት ያገኘ ከሆነ የውጤቱን ኮፒ ኦንላይን ያገኛል
- ሁሉም ተፈታኞች ውጤታቸውን የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፓርታል ላይ በመግባት User name እና Password በማስገባት ውጤታቸውን ማወቅ ይችላሉ።

**በትምህርት ሚኒስቴር በመተግበር ላይ ያሉ የሪፎረም ስራዎች**

በትምህርትና ሥልጠና ፍኖተ ካርታው(Ethiopian Education Development Roadmap:2018-2030) ላይ ቁልፍ ችግሮች ተብለው የተለዩትን ለማሻሻል በ2015 ዓ.ም የተጀመሩ የሪፎርም ስራዎች በዋነኝነትም የአጠቃላይ ትምህርት የስርዓተ ትምህርት ለውጥ፣የመጽሓፍት ዝግጅትና ሕትመት፣የ12 ኛ ክፍል ብሄራዊ

ትምህርትሚኒስቴር
MINISTRY OF EDUCATION

ፈተናን አሰጣጥና አስተዳደር፣ የትምህርት ቤቶችን ደረጃ የማሻሻል ፕሮግራሞች፣ዩኒቨርሲቲዎችን በተልዕኮና ትኩረት መስክ የመለየትና የማደራጀት፣ራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲዎችን የመደገፍ፣ለቅድመ ምረቃ ዩኒቨርሲቲ ተመራቂ ተማሪዎች የመውጫ ፈተና መስጠት፣የድህረ ምረቃ ትምህርት ፕሮግራም አመልካቾችን ብቃት ምዘና በያዝነው የ2016 ዓ.ም የትምህርት ዘመን ተጠናክሮ የሚሰራ ይሆናል፡፡

**የበለጠ መረጃ ለማግኘት**

ዌብሰይት: (moe.gov.et

ዌብ-ፖርታል: sip. moe.gov.et

ፌስቡክ: https://www.facebook.com/fdremoe


እሴተ የሺጥላ ከፍተኛ የኮሙኒኬሽን አማካሪ

ስልክ- 0911235322

ኢሜል--esete.yeshitla@ethernet.edu.et

አመለወርቅ ህዝቅኤል የህዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ስራ አስፈጻሚ

ስልክ 0911235322

ኢሜል-- ameleworkhizkeal@ethernet.edu.et